ጋዜጣዊ መግለጫ፡ በ2025 ዲዛይን ዊክ አዲስ አበባ የአስር አመት የዲዛይን ፈጠራን መዘከር
በአስቸኳይ የሚለቀቅ

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ – ጥር 9 2017 ዓ.ም

10ኛው የ የዲዛይን ዊክ አዲስ አበባ (DWAA) በምስራቅ አፍሪካ ለፈጠራ መድረክ የማይፋቅ አሻራ ትቶ በተሳካ ሁኔታ ተጠናቋል። ከጥር 1-4 ባማረ ሁኔታ የተካሄደው ይህ ፕሮግራም ቦሌ በሚገኘው ሲግኒቸር መኖሪያ እያደገ የሚገኘውን የኢትዮጵያ የፈጠራ ኢኮኖሚን ከማጉላት ባለፈ አዲስ አበባን የዲዛይን፣ የፈጠራ እና የባህል ማዕከል አድርጓታል።

## ለኢትዮጵያ የፈጠራ ኢኮኖሚ የለውጥ ምዕራፍ

የዚህ አመት ፕሮግራም ባህልን እና ፈጠራን በማጣመር ጥበብ፣ ፋሽን፣ ቴክኖሎጂ፣ ምግብ፣ ኢንቴሪየር ዲዛይን፣ ኪነ-ሕንጻን እና ሌሎችንም ማራኪ በሆነ መልኩ ለታዳሚዎች አቅርቧል። በአራት ቀናት ውስጥ ተሳታፊዎች የኢትዮጵያን ጥበብ እና ራዕይ የቃኙ ሲሆን ይህም DWAA ለስራ ፈጠራ እና ኢትዮጵያ ውስጥ የተሠሩ ምርቶች አለም አቀፍ መድረክ ላይ ያላቸውን ተደራሽነት በማሳደግ የሚጫወተውን ወሳኝ ሚና አጉልቶ አሳይቷል።

የዲዛይን ሳምንት አዲስ አበባ መስራች መታሰቢያ ዮሴፍ "የ10-አመት ጉዞአችንን ወደ ኋላ መልስ ብዬ ስቃኝ እና DWAA የጥበብ ባለሞያዎችን፣ ስራ ፈጣሪዎችን እና አለምአቀፍ ተመልካቾችን ወደሚያገናኝ መድረክነት እንዳደገ ሳስብ ኩራት ይሰማኛል" ስትል ተናግራለች። “በዚህ ዓመት ከሲግኒቸር መኖሪያ ቤት በአጋርነት መሥራታችን ኪነ ጥበብን፣ ዲዛይንን እና ፈጠራን በማቅረብ ወጥነን የተንሳነውን ዓላማ አሳክቷል።”

## ዓለም አቀፍ ተደራሽነት እና የሀገር ውስጥ ተጽዕኖ

ከዚህ በተጨማሪ DWAA 2025 የኢትዮጵያ የፈጠራ ኢንዱስትሪዎች ቱሪዝምን ለማሳደግ እና የሀገሪቷን የሪል እስቴት እና የዲዛይን ሴክተር ለመለወጥ ትልቅ ዕድል ይዞ እንደመጣ አስመስክሯል። እንደ ቻፓ፣ ያንጎ፣ አይስ አዲስ፣ ቀስተ ደመና፣ ቤንጎቴክስ እና ማራቶን ስፒሪትስ የመሰሉ አንጋፋ ድርጅቶች ጋር በአጋርነት መሥራታችን ዝግጅቱ የኢትዮጵያን የባህል ቱሪዝም እና የፈጠራ ሥራ ተደራሽነትን አንድ ደረጃ ከፍ አድርጎታል።

የፕሮግራሙ ዋና ዋና ገጽታዎች፡-

- ኤግዚቢሽኖች፡ በተለያዩ ዘርፎች የሚገኙ የሀገር ውስጥ እና የዓለም አቀፍ ዲዛይነሮች የተሰሩ ድንቅ ስራዎችን ታይተውበታል።
- ፓነሎች እና ወርክሾፖች፡ ከአዳዲስ የዲዛይን ፈጠራዎች እስከ ዘላቂነት ያላቸው የልማት ሥራዎች ባሉ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ከዘርፉ ባለሞያዎች ጋር ውይይት ተድርጓል።
- የኔትወርኪንግ ዕድሎች፡ የባህል መሪዎችን እና የስራ ፈጣሪዎችን በማገናኘት አብሮ የመሥራት ባህልን አበረታቷል።

ፕሮግራሙ በድንቅ ቲቪ ሰፊ የሚዲያ ሽፋን ያገኘ ሲሆን ይህም የጥበብ ባለሞያዎች እና የሥራ ፈጣሪዎች ይዘው የመጡትን ፕሮጀክት እና ልዩ ማንነት ለዓለም አቀፍ መድረክ በተገቢው መልኩ አድርሷል።

## የትብብር ጥሪ

DWAA ለሚቀጥሉት አሥር ዓመታት ደግሞ ከተለያዩ አጋሮች ጋር ለመሥራት ይፈልጋል። ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ደረጃ በሚኖራት የፈጠራ ኢኮኖሚ እድገት ላይ ከሚደግፏት ቁልፍ ተቋማት መካከል ማስተርካርድ ፋውንዴሽን፣ አፍሬክሲምባንክ፣ ሳፋሪኮም እና የኢትዮጵያ አየር መንገድ ናቸው።

መታሰቢያ "DWAA ባህል ተኮር ፕሮግራም ብቻ ሳይሆን የዲዛይን፣ የስራ ፈጠራ እና የአለም አቀፍ ትብብር መሪነቱን ያረጋገጠ ሲሆን ከቁልፍ አጋሮች ጋር በመተባበር ደግሞ የኢትዮጵያን የፈጠራ ኢኮኖሚ ተፅእኖ የበለጠ ማጎልበት እና በዓለም ዙሪያ ወዳሉ ማህበረሰቦች ተደራሽነቱን መጨመር ይቻላል" ስትል ተናግራለች።

## ቀጣዩ ምዕራፋችንን ይቀላቀሉ!

ፈጠራን፣ ትብብርን እና የባህል ተፅእኖን ለማጎልበት እና ወደር የለሽ ትኩረት በመስጠት ዲዛይን ዊክ አዲስ አበባ ለኢትዮጵያ እና ለአለም አቀፍ ዲዛይን ብሩህ ተስፋን ለመፍጠር ወጥኖ ተነስቷል።

አብረውን ለመሥራት የሚፈልጉ ከሆነ ወይም ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እኛን ማግኘት ከፈለጉ፦

ቤተል ብሩ
የህዝብ ግንኙነት አስተዳዳሪ

ኢሜል፡ designweekaa@gmail.com

ስልክ፡ (+251) 907-122- 414

(+251) 903-064-444